# ሰሞነኛ ቅፅ.2 ቁ.2

**<u>በአዲስ ዓመት</u>**

**<u>አዲስ ተስፋ፣አዲስ ዕድገት::</u>**

**በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ**

**ጄኔራል ጽ/ቤት**

**ነሀሴ/2001**

**August/2009**



**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd #308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: 213 365 6651 Fax: 213 365 6670**

www.ethioconsulatela.org

# በአዲስ ዓመት
# አዲስ ተሰፋ፣አዲስ ዕድገት፡፡

መስከረም ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የአዲስ ዓመት መባቻ ወር ነው፡፡ ሀምሌና ነሀሴ ጨፍኖ የከረመው የክረምት ደመና ለቀቅ ማለት ይጀምራል፡፡ ወንዞችና ጅረቶች የተሸከሙትን አፈርና ደለል አራግፈው ነጣ ማለት ይይዛሉ፡፡ ሜዳዎች፣ተራሮችና ሸንተረሮች ከዚህም ከዛም በሚፈነዱ ዕፅዋትና አደይ አበባዎች መዋብ ይጀምራሉ፡፡ እናም ፣ውብ መስከረም ለምለም ከነሙሉ ውበቱ የአዲሱን ዓመት ብስራትና ተስፋ ይዞ ብቅ ይላል፡፡

በመስከረም አዲሱ አመት የሰላም፣የብልፅግና፣የጥጋብና የፍቅር እንዲሆን ዘመድ ለዘመዱ፣መሪዎች ለህዝባቸው፣መገናኛ ቡዙሀን ለእድማጮቻቸው መልካሙን ይመኛሉ፡፡ መስከረም የእንኳን አደረሰን ሰላምታ መለዋወጫ ብቻ ሳይሆን የበጎ ምኞትና የብሩህ ተስፋ መግለጫ ወር ነው፡፡ አገር ቤት ያለው ህዛባችን በአካልና በዕውን ውጭ ያለው ወገን ደግሞ በነበር ትዝታ አስቦት ይውላል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ባለፈው አመት በርካታ የልማት፣የዴምክራሲና የሰላም ተግባራትን ያከናወነች ቢሆንም በዚሁ ልክ ቀላል የማይባሉ ፈተናዎችም ተቋቁማለች፡፡ በዓለማችን የተከሰተው ኢኮኖሚ ቀውስ ከምንታገለው ድህነት ጋር ተባብሮ የኑሮ ውድነትን እንዲያሻቅብ አድርገውት ከርመዋል፡፡ የኑሮ ውድነቱ በነባራዊ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን «የገብያ ግርግር .....» በሚጠብቁ አንዳንድ የገበያ ገማቾችና እህል ከዛኞች ንፉግነት ምክንያት ችግሩን ለመቅረፍ ጊዜ ወሳጅ አድርጎት ነበር፡፡ መንግስት በተለይ የምግብ እህል አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግና ጣራ የነካ የዋጋ መጠን ለመቋቋም እህል ከውጭ ገዝቶ በማስገባት ለህ/ሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲከፋፈል በማድረጉ የችግሩ ስፋት እንዲጠብ አድርጓል፡፡

**CONSULATE GENERAL OF ETHIOPIA**

**3460 Wilshire Blvd. Suite 308  Los Angeles, CA 90010**

ባለፈው ዓመት ግንባታቸው አልቆ ሀይል ማመንጨት ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ግዙፍ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ተቋሞች በወቅቱ አለመጠናቀቃቸው የሀይል እጥረትን ለማካካስ እንዲገዙ የታሰቡ የዲዝል ሞተሮች ፋይናንስ አቅራቢ የሆኑ አለምአቀፍ ተቋሞች በፈጠሩት ሳንካ ምክንያት መግዛት ባለመቻሉ የሀይል ዕጥረቱን ውስብስብ ከማድረግ አልፎ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎቻችን ላይ ጫና ማሳረፉቸው አሌ አይባልም።እነዚህና ሌሎች መለስተኛ ችግሮች ያጋጠሙ ቢሆንም በተሸኘው ዓመት ለዘለቄታ ሰላማችንና ዕድገታችን ተዋፅዖ ያደረጉ የመሰረት ልማት ስራዎች ተከናውነዋል። ለአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ መሻሻሎች ፈር የቀደዱ ተግባራትም በስራ ላይ ውለዋል።

በ2001 አገራችን በተለይ በትላልቅ ከተማዎች ግዙፍ ግንባታዎች ተገንብተው ተመርቀዋል።በአዲስ አበባ የቀለበት (የሽግግር መንገድ) ተመርቆ በስራ ላይ የዋለ ሲሆን የከተማዋን ደረጃ የሚጠብቁ መንገዶች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ። በተለያዩ ክልሎች ዋና እና መጋቢ የሆኑ ደረጃቸውን የተጠበቁ መንገዶች ተሰርተው በአገልግሎት ላይ ውለዋል። ግዙፎቹ የሀይድሮ ኤልክትሪክ ግንባታዎች የተወሰኑት የሙከራ ምርት የጀመሩ ሲሆን ሌሎች የማጠቃለያ ጥቃቅን ተግባራት ብቻ የሚቀራቸው ናቸው።አሁን በተያዘው መልክ ተከዜ በሙሉ አቅሙ ወደ ተግባር ሲገባ፣ የጊቤ 2 እና የጣና በለስ የሀይል ማመንጫ ጣቢያዎች ስራ ሲጀምሩ እየተቆራረጠ ሲያስቸግረን የነበረው የኤሌክትሪክ አቅርቦት ባስተማማኝ መልክ አቅርቦቱ እንደሚስተካከል ይጠበቃል።

በአገራችን የመልካም አስተዳደር ተግባራትን ከችግር በፀዳ መልክ ለማከናወን ዘመናዊ የስራ አመራርና አስተዳደር ስልቶች ተነድፈው ባለፈው ዓመት በመንግስት መ/ቤቶች ተግባራዊ መሆን ጀምረዋል።አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎችን ስራ የማሳለጥና የውጤት ፋይዳቸው በእየጊዜው እየተመዘነ ለመልካም አስተዳደር መደላድል ይሆኑ ዘንድ በተግባር ላይ በመዋል ይገኛሉ።

እንደሚታወቀው በመጪው አመት በአገራችን ብሄራዊ ምርጫ ይካሄዳል። ይህ ምርጫ የዲሞክራሲ ስርዓት እሴቶች እንዲጠናከሩ የተጀመሩ የልማትና የዕድገት ክንውኖች እንዲዳብሩ የኢትዮጵያ ህዝቦች የሰብአዊና ዲሞክራሲያው መብቶች ይበልጥ

ስር እንዳይሰዱ ሰላማዊው ህገመንግስታዊ ስርዓት እንዲዳብር ከሁሉም በላይ ምርጫው አገራችን የጀመራቻቸውን የዕድገትና ልማት የዕውቀትና የቴክኖሎጂ አቅም የሚያጠናክር እንደሚሆን ይጠበቃል።

የ2002 ዓመት ምርጫ በዕኩልነት በፍትሀዊና ርዕታዊነት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን በሰላማዊና በዲሞክራሲያዊ የምርጫ ውድድር እንዲሁም በሰለጠነ የፖለቲካ መስተጋብር የሚያምኑ ኃይሎች ሁሉ ሙሉ ተሳትፎን ይጠይቃል።

በሰላማዊ የፖለቲካ ተርክቦት ፅኑ ዕምነት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራችን ስራ የመትከላቸውን ያህል አሁንም ከአጉራጠንና ከአመፃ የፖለቲካ ሕመም ያልሻሩ እንዲሁም «በአቋጥሩኝ» የፖለቲካ አዙሪት በውጭ አገር ይባክኑ ዘንድ የወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች ሰለማዊውን የፖለቲካ አካሄድ ቢቻላቸው ለማወክ ካልሆነም የአጥቋሪነት ዘመቻ ለማካሄድ ዕቅድ ነድፈዋል። የስራ ስምሪት ድልድልም ነቅሰው አውጥተዋል። የዱቤ ፀሀፊዎችንም ገዝተዋል። በምርምርና በጥናት ላይ ለተመሰረተ አስተያየት ደንታ ለሌላቸውና ከአባይ ጠንቋይ ለማይተናነሱ የውጭ አገር የፖለቲካ ገማቾችም ቀብድ ሰጥተዋል። በአመፅ ሀይል ነፃ ስናወጣችሁ የምንመልስላችሁ ግብር ክፈሉ በማለት ካርኔ የማይሰጥበት የገንዘብ ከረጢት ይዘው መዞር ጀምረዋል።

የአገራችን የዲሞክራሲና የሰላም እርምጃ በህዝባችን የተባ ተሳትፎ እንዲሁም ሰላማዊና የሰለጠነ የፖለቲካ ባህልን መርሀቸውና መመሪያቸው አድርገው በወሰዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዋንኛነት የሚወሰን ቢሆንም ለስልጣን ኑፋቄ ሲሉ ግርግር የሚመኙ በውጭ የተደራጁ የፖለቲካ ወፈፊዎች ወቅትና ዘመን ቆጥሮ የሚንጣቸው የፖለቲካ ግርሻት አሁንም የተነሳባቸው በመሆኑ ይህ ዘዴያቸው ጊዜው ያለፈበት መሆኑን በመግለፅና በቁርጠኝነት ልንገልፅላቸው ብሎም ልንታገላቸው ይገባል።

በመጨረሻም መጪው አመት የሰላም፣ የእድገት፣ ብልፅግናና የብሩህ ተስፋ መሰነቂያ ዘመን እንዲሆን ልባዊ ምኞታችን እንገልፃለን።

**CONSULATE GENERAL OF ETHIOPIA**
**3460 Wilshire Blvd. Suite 308 Los Angeles, CA 90010**